# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## በግብርና ሚኒስቴር

## የኢትዩጵያ ደን ልማት

## የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ

## ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት /2015
አዲስ አበባ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# በግብርና ሚኒስቴር

# የኢትዩጵያ ደን ልማት

# የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ ደን ልማት የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢትዮጵያ ደን ልማት ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣

- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የኢትዮጵያ ደን ልማት ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በባለስልጣኑ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡
የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

## ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. ከስራ ለለቀቁ ሰራተኞች ብር 1,207.00 ያለአግባብ የተከፈለ መሆኑ፤
2. የተመራማሪ I ጥቅማጥቅም ብር 46,000.00 መከፈል ሲገባው ብር 94,000.00 በመክፈሉ በልዩነት ብር 48,000.00 በሂሳብ መደብ 2111201 ያለአግባብ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤
3. ለአስተዳደር ዳይሬክተሮች የኃላፊነት የጥቅማ ጥቅም አከፋፈል ከመንግስት የተፈቀደበት ደብደቤ ወይም መመሪያ ሳይኖር በተጨማሪም ተመራማሪዎች የኃላፊነት አበል የማይመለከታቸው መሆኑን እየታወቀ በድምሩ ብር 185,000.00 ያለአግባብ የተከፈለ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 3 ከተገለጸው በስተቀር የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት ትክክለኛውን ገጽታ ያሳያሉ፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

## I. <u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች (Emphasise Matters)</u>

1.1. የፓወር ፖይንት ማቀፊያ ፓይንተር በሂሳብ መደብ 2211102 የቢሮ ዕቃዎች መያዝ ሲገባው በሂሳብ መደብ 2221103 የመስተንግዶ ወጪ የሂሳብ አርዕስት ብር 2,530.00 የተመዘገበ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

## II. <u>የህጋዊነት ጉዳዮች (Compliance Matters)</u>

2.1 የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ሄደው ለመማር በገቡት የውል የጊዜ ገደብ ውስጥ ትምርታቸውን አጠናቅቀው ወደ ስራቸው ያልተመለሱ እና በገቡት ውል መሰረት ሳያገለግሉ ወይም በድምሩ ብር 306,652.00 መክፈል ሲገባቸው ሳይከፍሉ የለቀቁ መሆኑ፤

2.2 በሰኔ30/2014 በሚታየው ሂሳብ ሪፖርት በድምሩ ብር 385,313.74 ወቅቱን ጠብቆ ያልተሰበሰበ ሂሳብ መሆኑ፤

2.3 በድምሩ ብር 2,019.05 ወቅቱን ጠብቆ ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ የሚታይ መሆኑ፤ታውቋል፡፡

## III. <u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)</u>

### 3.1 <u>የንብረት አያያዝን በተመለከተ</u>

መመሪያው በሚያዘው መሰረት አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ተሰብስበው ስልጣን በተሰጠው በመንግስት አካል መወገዳቸውን እንዲሁም ለንብረቶች ተገቢው ጥገናና እንክብካቤ መደረጉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ

- በዋና መ/ቤት አገልግሎት የማይሰጡ እና ያልተወገዱ ንብረቶች መኖራቸው፤

አቶ ብርሃኔ አሳየኸኝ የተባለ ግለሰብ በቀን 02/12/2013 በፃፉት ደብዳቤ ለስራ የተረከቡት ላፕቶፕ ኮምፒውተር ስለጠፋብኝ ማስረከብ አልቻልኩም ብለው በማመልከት ዋጋ አጥኚ ኮሚቴ ተቋቁሞ ዋጋ ያጠና ቢሆንም በተጠናው መሰረት ሳይሆን የላፕቶፑን የመዝገብ ዋጋ አንድ አራተኛ እንዲከፍል በኮሚቴው በተወሰነለት መሰረት ብር 4,000.00 ብቻ በቀን 26/07/2014 በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 350772 ገቢ ያደረጉ ሲሆን የንብረቱ የመዝገብ ዋጋ ብር 15,687.00 ሲሆን በልዩነት ብር 11,687.00 በቀሪ የሚፈለግ መሆኑ፤

3.2 በምርታማነት ማሻሻያ 17 ተሽከርካሪዎች የተመዘኑ ሲሆን ቀሪዎቹ 36 ተሽከርካሪዎች ያልተመዘኑ ወይም ኬሎ ሜትር ምዘና የሌላቸው መሆኑ፣

3.3 የኢትዮጵያ ደን ልማት የ38 መኪኖች የባለቤትነት ማረጋገጫ መታወቂያቸው በሌላ ተቋም ስም የሚገኝ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

3.4 **የፌዴራል** ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምሰት አንቀጽ 17/3 መሰርት ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት ባለፉት በጀት ዓመታት የኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት በመ/ቤቱ እርምጃ ያልተወሰደባቸው፡-

- መ/ቤቱ ለሰራተኛዋ የተመራማሪ I ጥቅማጥቅም የቤት ኪራይ 4,000፣ የሞባይል ስልክ 300 እና የኢንተርኔት አገልግሎት 300 ብር በድምሩ ብር 4,600.00 መከፈል ሲገባው ያለአግባብ የቤት ኪራይ 8,000.00፣ የኃላፊነት አበል 2,000.00፣ የሞባይል ስልክ 700፣ የኢንተርኔት 700 እና የውሎ አበል 800 በድምሩ ብር 12,200.00 በመክፈሉ የተነሳ በልዩነት ብር **7,600.00** ያለአግባብ በብልጫ የከፈለ መሆኑ፣
- በመ/ቤቱ አስራ ሁለት(12) ለሚሆኑ ዳሬክተሮች የኃላፊነት አበል የማይመለከታቸው መሆኑን እየታወቀ በሂሳብ መደብ 2111201 በተለያዩ የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር ብር 207,000 የተከፈለ መሆኑ፤
- መ/ቤቱ የለቀቁ 5 ሰራተኞች ያለአግባብ የተከፈላቸው ደመወዝ ብር 8,242.14 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

**የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት**

**መጋቢት/ 2015**